የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ
መታሰቢያ ድርጅት

ቁጥር ____________

ቀን ሚያዝያ 16, 1991 ዓ.ም

ማስታወሻ

የጠቅላላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎት በመረዳት በንጉሣዊ ቤተሰብ ስምምነትናሙሉ ፈቃድ በ1997 ዓም የተመሠረተውን የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት የሥራ ሂደት በተመለከተ በጽሑፍና በመልክተኞችም በኩል በየጊዜው ያቀርብናቸውን መልዕክቶች በትሕትና እናስታውሳለን። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ድርጅቱ በተጠና የሥራ ዕቅድ መሠረት ተግባሩን ለመፈጸም በመትጋት ላይ እንዳለ የድርጅቱን መመሥረቻ ደንብ በማስመዝገብ በኩል ችግር ስለገጠመው በአቀደው ፍጥነት መራመድ ተስኖት ለማዘገም ተገድዶ እንደነበረም የሚታወስ ነው።

ይሁን እንጂ የድርጅቱ ዓላማ ክቡር፤ የሚያንቀሳቀሱትም ፍትሕና ሰላም ኃይል ስለሆኑ በዚህ ቁም ነገር ላይ በማተኮር ችግሩን በዜና ማሰራጫ አማካይነት ለሕዝብ በማወያየትና ለመዘጋቢው የመንግሥት መሥሪያ ቤት አቤቱታና ተጨማሪ ማብራሪያ በማቅረብ በመጨረሻው መልካም ፍጻሜ ላይ ለመድረስ ተችሏል። በሌላ አገላለጽ የድርጅቱ ሕጋዊ ሰውነት ታውቆ አሁን በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል ለማለት ነው።

ድርጅቱ በአንድ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እየተመራ ለልዩ ልዩ ተግባሮች አፈጻጸም የተመደቡ ሰባት ኮሚቴዎች ተዋቅረው በአንድነት የሚንቀሳቀሱት ሶስት ዕቅዶች ለመፈጸም ነው።

የመጀመሪያው ዕቅድ የባለውለታውን የቀድሞውን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴን አጽም በጊዜያዊው ስምምነት መሠረት አሁን ካለበት ከታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ገዳም ወደ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አዛውሮ በተሰናዳው መካነመቃብር በሚገባው ክብርና ሥነስርዓት ማሣረፍ ነው። የዚህን አሠራር ሂደት በቅርብ ሆኖ በጥንቃቄ ላልተመለከተው ቀላል መስሎ ይታይ ይሆናል። ሥራው በዕለቱ የሚጠበቁትን ቅድመ ሁኔታዎች ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን የታጎለውን ፍትሕ ማስተካከልና ታሪካዊነቱን ማረጋገጥ ስለሚገባ ልዩ ጥንቃቄን የሚጠይቅ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። ከዚህም በላይ በበዓሉ አከባበር በውጭ አገር የሚገኙ የግርማዊነታቸው ወዳጆች በእንግድነት የሚገኙበት፤ ከኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ከየክፍሉ የተውጣጡ ተጠሪዎች በእንግዳ ተቀባይነት የሚሳተፉበት ስለሆነ መሰናዶው ከበዓሉ ትልቅነት ጋር እንዲስማማ ማድረግ ያስፈልጋል።

በሥነስርዓቱ የሕዝብን ሙሉ ተሳትፎ ለማረጋገጥ የቀብሩ ሥነስርዓት በሕዝብ በዓልና ከግርማዊነታቸው ጋር በተያያዘ ቀን እንዲሆን የሚመረጥ ሲሆን የግርማዊነታቸው ልደትና የዘውድ በዓል ቀናት አፈሲየል የሕዝብ በዓላት ባለመሆናቸው በነዚህ ቀናት የቀብሩን ሥነስርዓት ለመፈጸም አዳጋች ይሆናል። የልደት ቀናቸውም ሆነ ያረፉበት ቀን በአጋጣሚ በበዓል ቀን ቢውልም እንኳ የክረምት ጊዜ በመሆኑ ለበዓሉ አከባበር አመቺ አይሆንም። ስለሆነም የቀብሩን አፈጻጸም ሚያዝያ 27 ቀን ማድረጉ አማራጭ ስለሌለው ሚያዝያ 27 ቀን 1992 ዓም እንዲፈጸም በመታሰቢያ ድርጅቱ ታቅዷል።

አጽሙ በክብር የሚዛወርበትን ሥነስርዓት በሚመለከት አማራጭ ዕቅዶች በዝርዝር ተነድፈዋል። የዝግጅቱን ክብደት ግንዛቤ እንዲሰጥ ያህል መነሻ ፕሮግራሙ ከዚህ ደብዳቤ ጋር በአባሪነት ተያይዟል። ለሥነስርዓቱም ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገው ወጭ በዝርዝር እየተጠና ቢሆንም ወጭው አምስት ሚሊዮን ብር አካባቢ እንደሚደርስ ተገምቷል።

ሁለተኛው ዕቅድ በጠቅላላ አነጋገር ሲገለጽ ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኀይለሥላሴ ለአገራቸው አንድነትና ክብር፣ እንዲሁም ለሕዝቡ ደኅንነት በፈታኝ ጊዜና በሰላም ጊዜም ለፈጸሙት የረጅም ጊዜ የመሪነት አገልግሎት በተለይ በኢትዮጵያ ትምህርትን በማስፋፋት በኩል ላበረከቱት ታላቅ ድርሻ ቀዋሚና ሕያው መታሰቢያ እንዲሆን በሥማቸው የሚጠሩ የከፍተኛ ትምህርት እድገት መርጃ የሚሆኑ የስኮላርሽፕ ተቋምና ቤተመጻሕፍት ወመዘክር ማዕከሎች ማቋቋም ነው። ይህ ዕቅድ ከፍትሕ ወዳዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ የረጅም ጊዜ ፍላጎት ጋር የሚስማማ ከመሆኑም በላይ ጥቅሙ ለትውልድ የሚተላለፍ ነው።

የፕሮጀክቶቹን ዝርዝር ሃሳብ በማብራራት የተዘጋጁት ሰነዶች በልዕልት ሰብለ ደስታ በኩል አስቀድመው የተላኩ ሲሆን ዋና ዋና ሃሳቦቸው እንደሚከተለው ነው።

1. የስኮላርሽፕ ተቋሙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው በከፍተኛ ውጤት ከተመረቁ በኋላ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ከፍተኛ ትምህርታቸውን በኮሌጅና በዩኒቨርሲቲዎች ለመከታተል ችግር ለገጠማቸው ተማሪዎች ስኮላርሽፕ በመስጠት ችግራቸውን ያቃልላል።
2. ቤተመጻሕፍት ወመዘክር ማዕከሎች ለሕዝብ አመቺ በሆኑ ከአዲስ አበባ ውጭ ከፍተኛ ጥቅም ሊሰጡ ይችላሉ በሚባልበት አካባቢዎች እየተቋቋሙ ለዕውቀት ማስፋፊት፣ ለታሪክና ባሕል ግንዛቤና ቅርስነት የሚያገለግሉ ጠቃሚ ሰነዶች ማሰባሰቢያ የሚሆኑ ናቸው። ማዕከሎቹ የሕዝቡን የማንበብ ፍላጎት የሚያነሳሱና የሚያረኩ እንዲሆኑ ከመታሰቡም በላይ በማኅበረሰቡ ልዩ ልዩ ክፍሎች መካከል ጤናማ ግኑኝነት እንዲፈጠር ይረዳሉ ተብሎ ታምኖበታል።/.

ሶስተኛው ዕቅድ በአዲስ አበባ የግርማዊነታቸውን ታላቅ ታሪክ የሚገልጹ በሕይወታቸው ዘመን የነበሩ ቅርሳቅርሶችን፣ ሰነዶችንና የመሳሰሉ በማሰባሰብ አንድ የተሟላ ቤተመጻሕፍት ወመዘክር ለማቋቋም ወደፊት ሰፊ ጥናት ማድረግ ነው።

የግርማዊነታቸውን አጽም በክብር ለማዘወር ከሚያስፈልገው ወጭ በተጨማሪ ለስኮላርሺፕ ተቋሙ ብር 10,000,000 (አሥር ሚሊዮን) በመመደብ በወለዱ በየዓመቱ ለሃያ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ትምህርታቸውን እስኪያጠናቅቁ ስኮላርሺፕ ለመስጠት ታቅዷል። እንዲሁም ከኢትዮጵያ ዕድገት ጋር የተያያዘ ጥልቅ ምርምር ለሚያካሂዱ አራት ምርጥ ድኅረምሩቃን ማበራታቻ በየዓመቱ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ወጭ ለማድረግ ታስቧል። ከአዲስ አበባ ውጭ በአሥር ልዩ ልዩ ከተሞች የቤተመጻሕፍት ወመዘክር ማዕከሉችን ለማቋቋም ብር 10,000,000 (አሥር ሚሊዮን) በመመደብ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) ለማዕከሉቹ ሕንጻ ሥራ ዕርዳታና በመጀመሪያ ለሚፈለጉት መጻሕፍትና ቅርሳ ቅርሶች ማሰባሰቢያ የሚውል ሲሆን ከቀሪው ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) የሚገኘው ወለድ የሥራ ማስኬጃና ተጨማሪ መጻሕፍቶችንና ቅርሳ ቅርሶችን ለመግዣ ወጭን እንዲሸፍን ይደረጋል።

የግርማዊነታቸውን አጽም በክብር ማሳረፍ ሥነስርዓት ጋር በማቀናበር የስኮላርሺፑ ተቋም ሥራ መጀመር በዕለቱ ለሕዝብ የሚገለፅ ሲሆን የቤተመጻሕፍት ወመዘክር ማዕከሉች መሠረት ድንጋይ የማኖር ሥነስርዓትም በዚያው ሳምንት ውስጥ እንዲከናወን ታቅዷል።

ከላይ የተዘረዘሩትና ሌሎችም ለአገር ጠቃሚ የሆኑ በግርማዊነታቸው ሥም የሚቋቋሙ መታሰቢያዎች በተግባር እንዲውሉ በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ ፍትሕ ርትዕ ወዳድ ከሆነ ወገን ሁሉ የንብረትና ገንዘብ ሰፊ ድጋፍ ማግኘት አስፈላጊ ስለሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደኅንነትና ለአገር ዕድገት እንዲሁም ለአፍሪካና ለዓለም ሰላም ግርማዊነታቸው በረጅም የመሪነት ጊዜያቸው ያበረከቱትን ከፍተኛ ድርሻ በሰፊው በመግለጽ የዚህ ሃሳብ ደጋፊ ይሆናሉ ብለው ከሚያምኑባቸው ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና መንግሥታት የንብረት፣ የገንዘብና የሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ ዕርዳታዎች እንዲያስገኙልን በማሳሰብ በታላቅ ትሕትና ይህን ማስታወሻ ልከናል።

ከአክብሮት ሰላምታና በጎ ምኞት ጋር

ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት
የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ